# የፓለቲካ ፓርቲዎችን ክራሞት

ኢዛና ዘ መንፈስ 12-06-17

ዴሞክራሲ በመባል የሚታወቀው የስርዓተ መንግስት አስተዳደራዊ ዘይቤ፤ የህዝብን ፍላጎት በማሟላት ረገድ የተሻለው አማራጭ መንገድ ስለመሆኑ ተደጋግሞ የተነገረ ጉዳይ ነው። በተለይም እንደ ኢትዮጵያ እጅግ በርካታ የብሔር ብሔረሰብ ህዝቦች ለሚገኙባቸው ሀገራት ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን የመገንባት አስፈላጊነት፤ የህልውና ጉዳይ እንጂ ምርጫ አይደለም ተብሎ ይታመናል። ይህ የሚሆንበት ዋነኛ ምክንያት ደግሞ፤ የየራሳቸው ብሔራዊ፤ ወይም ብሔረሰባዊና ሃይማኖታዊ ብሎም ስነልቦናዊ ማንነት ላይ የተመሰረተ ህውልና ያላቸው በርካታ ህዝቦችን አቅፎ በያዘ አንድ ልዑላዊ ሀገር ውስጥ፤ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ማስፈን ካልተቻለ በስተቀር፤ የብዝሃነት መገለጫ ተደርገው የሚወሰዱ ሕብረ ብሔራዊ የጋራ እሴቶችን በአግባቡ ማስተናገድ ያዳግታል ተብሎ ስለሚታመን ነው ማለት ይቻላል።

ይሄን መሰረተ ሃሳብ በሚያዳብር ፓለቲካዊ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የየራሳቸውን ተራማጅ አቋም የሚያንፀባርቁበትን ትንተና ሲሰጡ ከምናውቃቸው የሀገራችን ምሁራን መካከል አንዳንዶቹ እንደሚሉት ከሆነም፤ የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ አስፈላጊነት ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር እየተገናዘበ መታየት እስካልቻለ፤ እንዴትና ምን ዓይነት ሀገራዊ የጋራ መግባባት ላይ መድረስ እንደሚቻል መገመት እንኳን ያስቸግራል። ይህን የመከራከሪያ ነጥብ በማንሳት ረገድ የሚታወቁት ኢትዮጵያውያን የፓለቲካ ተንታኞች የሚመሳሰሉበት አንድ መሰረታዊ ጉዳይም፤ መላው የሀገራችን ብሔሮች፤ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ከአፄው ዘመነ መንግስት ጀምሮ፤ በተለያየ አግባብ የሚገለፅ ፀረ ጭቆና ትግል ሲያካሂዱ የቆዩበትን የዴሞክራሲያዊ መብት ጥያቄ ስለ መመለስ አስፈላጊነት ያላቸው ፅኑ አቋም ነው ማለት ይቻላል። እናም ከዚሁ እምነታቸው በሚመነጭ ተራማጅ የፓለቲካ አመለካከት ላይ ተመስርተው ይበጃል የሚሉትን ሃሳብ ሲሰነዝሩ "ኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ስለመገንባት አስፈላጊነት ጉዳይ የሚናገር ማንኛውም አካል ቢሆን ብዝሃነትን በአግባቡ ማስተናገድ እንደሚጠበቅበት መዘንጋት የለበትም" ነው የሚሉት ተንታኞቹ።

በሌላ አነጋገር፤ ኢትዮጵያ ከሰማኒያ በላይ ብሔር፣ ብሔረሰብና ህዝቦች የሚኖሩባት ሀገር ሆና ሳለ፤ ይህን ድፍን የዓለም የማህበረሰብም ጭምር አሳምሮ የሚያውቀውን ነባራዊ ጥሬ ሀቅ ለማስተባበል ሲቃጣቸው የሚስተዋሉ የፓለቲካ ፓርቲዎች ስለዴሞክራሲ አስፈላጊነት የመናገር ሞራላዊ ብቃት ሊኖራቸው አይችልም እንደማለት ተደርጎ የሚወሰድ አንድምታ ያዘለ ነው ትንታኔያቸው፣

በእርግጥም ደግሞ  እንደ ኢትዮጵያ የበርካታ ብሔሮች፤ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የጋራ ህልውና የተመሰረተባት ሀገር ውስጥ ለሌሎች የብሔራዊ ማንነት ጥያቄ ተገቢ ዕውቅና መስጠትን እንደ ውርደት የሚቆጥሩና ብዝሃነትን ለማስተናገድ የሚያስችል ሕገ መንግስታዊ ማእቀፍ መኖሩን አምርረው በመቃወም የሚታወቁ ፓለቲከኞች፤ ስለዴሞክራሲያዊ አንድነት ጠቀሜታ (አስፈላጊነት) ጉዳይ እያነሱ

የሚደሰኩሩበትን የሞራል ብቃት ከወዴት እንዳገኙት ጥያቄ የሚያጭር ጉዳይ ነው። እንግዲያውስ እኔም የፓለቲካ ፓርቲዎቻችን ክራሞት በሚል ርዕሰ ይህቺን አጭር ጽሁፍ ለመጫጫር ስል ብዕር ከወረቀት ማገናኘቴ ያለ ምክንያት አይደለም። ይልቅስ የዛሬ ዓመት ገደማ በኢህአዴግና በተቃዋሚ የፓለቲካ ፓርቲዎች መካከል ስለተጀመረው የድርድር መድረክ ሂደት አንስቼ በተለይም የቅርብ ጊዜ ክራሞታቸውን የሚመለከት አስተያየቴን እስነዝር ዘንድ ተገቢ መስሎ ስለተሰማኝ እንጂ።

ስለሆነም አሁን በቀጥታ ወደዋናው ነጥብ አልፌ ኢህአዴግና አስራ ስድስት ያህል ተቃዋሚ ፓርታዎች ከአንድ ዓመት ላላነሰ ጊዜ ሲያካሂዱ የቆዩት ፓለቲካዊ ድርድር ወይም ውይይት ዛሬ ላይ ምን ተጨባጭ ውጤት እያመጣ ይሆን? እውን ፓርቲዎቹ ላለፋት ሁለት አስርት ዓመታት የታዘብነውን ፖለቲካዊ እሰጥ - አገባና እንዲሁም ደግሞ አላስፈላጊ ፍጥጫ የሚያስቀር መፍትሔ ለማበጀት ችለዋልን? ወይስ አሁንም እንደተለመደው ሁሉ አንዱ ሌላውን በጠላትነት ዓይን እየተመለከተ ሲወነጅለው የምንሰማበትን ጭፍን መወጋገዝ የማስቀጠል አዝማሚያ እንዳለ ነው? ወዘተ ለሚሉ ጥያቄዎች የሚያጠግብ ምላሽ የማፈላለግ ጥረት ለማድረግ እሞክራለሁ።

ስለዚህም እንደኔ ትዝብት ከሆነ፤ ኢህአዴግን ጨምሮ አስራ ሰባት ያህል ሀገር አቀፋዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሳተፉበትና ከአንድ ዓመት ላላነሰ ረጅም ጊዜ ሲካሔድ የቆየው የውይይትና የድርድር መርሐ-ግብር፤ በእርግጥም ተስፋ ሰጭ በጎ ጅምሮችን ያየንበት ፖለቲካዊ የጋራ መድረክ ተደርጎ ቢወሰድ የሚበዛበት አይመስለኝም። ምክንያቱም፤ ደግሞ ፓርቲዎቹ የበለጠ ትኩረት ሰጥተው በስፋትና በጥልቀት የመከሩባቸው አብዛኞዎቹ የጋራ ጉዳዮች፤ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግርን መሰረት ያደረገ የመድበለ ፓርቲ ፖለቲካዊ ትግል እየጎለበተ እንዲቀጥል የማይናቅ አዎንታዊ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ጠቃሚ ነጥቦችን ያካተቱ ሆነው እንዳገኘኋቸው ማስረዳት እችላለሁና ነው።

ለአብነት ያህልም፤ ለሰላማዊ የፖለቲካ ስልጣን ሽግግር ባህል መደበር ወሳኝ የሚባል ገንቢ ሚና ሊጫወቱ እንደሚችሉ ከሚታመንባቸው የዴሞክራሲ ተቋማት መካከል አንዱና ምናልባትም ዋነኛው ተደርጎ ሊወሰድ የሚችለውን የምርጫ ሕጋችንን አጠቃላይ ይዘት እያነሱ በመመርመር ረገድ ፓርቲዎቹ ከዚህ ቀደም እንብዛም ያልተለመደ ዓይነት ዕርስ በርስ የመደማመጥና የመተማመንም ጭምር በጎ አዝማሚያ ስለማሳየታቸው ነው መረጃዎች የሚጠቁሙት። ከዚህ የተነሳም የበርካታ ወራትን ሂደት በጠየቀ ተከታታይ ውይይትና ድርድር አማካኝነት ያለምንም የአንድ ወገን አሉታዊ ተፅእኖ መክረው - ዘክረው ሲያበቁ፤ የተስማሙባቸው ነጥቦችን መጥቀስ ይቻላል። ሀገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲዎቹ የምርጫ ሕጉ ላይ አሉ ስለሚሏቸው ጠንካራም ሆነ ደካማ ጎኖች ጉዳይ የየራሳቸውን ምክንያታዊ መከራከሪያ እያቀረቡ ስለሚቃወሙት አልያም ደግሞ ስለሚደግፋት የምርጫ ሕጉ ድንጋጌ በበቂ ማብራሪያ የተደገፈ ሃሳብ ሰጥተዋል። ሃሳባቸው ነጥሮ ሲወጣና ስለሚኖረው ሀገራዊ ጠቀሜታ አብዛኛው የመድረኩ ተሳታፊዎች እንደተስማሙበት ተቆጥሮ ሲያልፍ የታየበት አግባብም ነው ያለው። በዚህ መሰረትም፤ ፌደራላዊት፤ ዴሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ እስከ ዛሬ ድረስ ትከተለው የነበረውን <<ሃምሳ አንድ ለሃምሳ>> በመባል የሚታወቅ ዓለም አቀፍ ተቀባይነትን ያገኘ አማራጭ የምርጫ ሂደት

ማስፈፀሚያ ሕግ በሌላ <<ቅይጥ ትይዩ>> ተብሎ በሚጠራ ዓለም አቀፍ የምርጫ ሕግ እንዲተካ ስምምነት ላይ ስለመድረሳቸው ታውቋል ፓርቲዎቹ።

እንዲሁም ደግሞ ከዚህ ቀደም በነበረው የኢትየጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሕገ ደንብ ላይ <<የፖለቲካ አንድ ፓርቲን ለመመስረት ፈልገው ተነሳሽነቱን የሚወስዱ ሰዎች፤ ቢያንስ ሁለት ሺህ ዜጎችን በመስራች አባልነት ማስፈረም ይኖርባቸዋል>> ይል የነበረውን ድንጋጌ << ቢያንስ የሶስት ሺህ ሰዎችን ፊርማ አሰባስቦ በመስራች አባልነት ማስመዝገብ ይጠበቅባቸዋል>> ተብሎ እንዲሻሻል ፓርቲዎቹ መክረው፤ ዘክረው ስምምነት ላይ ስለመድረሳቸው የታመኑ ምንጮች አመልክተዋል። እነዚህን የመሳሰሉ ተጨባጭ የሕጋዊ ድንጋጌ ማሻሻያ የተደረገባቸው ነጥቦችን  በሚመለከት ግልፅና የማያሻማ የጋራ አቋም ለመያዝ ያስቻላቸውን ተከታታይ የውይይትና የክርክር ሂደት ለአንድ ዓመት ያህል አስቀጥለው፤ ከዚህ ቀደም ምንም ዓይነት የጋራ ርዕሰ ጉዳይ የሌላቸው ያህል ከሩቅ የጎሪጥ እየተያዩ ሲወጋገዙ ብቻ ለሚያውቃቸው ኢትዮጵያዊ ህብረተሰብ ዘለቄታዊ ዕጣ ፈንታ ይበጃል የሚሉት ሀገራዊ አጀንዳ ዙሪያ ዕርስ በርስ የመነጋገርን አስፈላጊነት ያመላከተ ፖለቲካዊ ክራሞታቸውን ላሳዩን የመድረኩ ተሳታፊ ፓርቲዎች በሙሉ አድናቆቴ ልባዊ ነው።

እንደኔ ግንዛቤ ከሆነ መቸስ መላው የሀገራችን ብሔሮች፤ብሔረሰቦችና ህዝቦች በእጅጉ የሚመሳሰሉባቸው በርካታ መሰረታዊ የጋራ ጉዳዮች ስለመኖራቸው፤ እንኳንስ አንድን የፖለቲካ ፓርቲ የመምራት ሃላፊነት የመሸከም አቅም አለው ተብሎ ለሚገመት ዜጋ ለተራው ኢትዮጵያዊ አርሶአደርም የተሰወረ አይደለም ባይ ነኝ። ምክንያቱም ደግሞ እኛ የዚች ሀገር ምልዓተ ህዝቦች እንደ አንድ ህብረተሰብ በሌላው ዓለምም ጭምር የምንታወቅባቸውና አድናቆትን ያተረፉልን የጋራ ማንነታችን ጉልህ መገለጫዎች ያሉን ስለመሆናቸው ለመረዳት ያን ያህልም ዕውቀት የሚያስፈልገው ጉዳይ ተደርጎ አይወሰድምና ነው። በግልፅ አነጋገር፤ የኢትዮጵያውያን ህዝቦች የጋራ ማንነት መገለጫ የሆነውን ህብረብሔራዊነታችንን እንደ ልዩ ተፈጥሯዊ ፀጋ ተቀብለን፤ የዚያኑ ያህልም ብዝሃነትን በአግባቡ ለማስተናገድ የሚያስችለንን ዴሞክራሲያዊ የሀገር አንድነት ገንብተን፤ ህልውናችን በጥብቅ ታሪካዊ፤ ማህበራዊ፤ መልክዓ ምድራዊና ስነ ልቦናዊ ቁርኝቶች የተሳሰረበትን የአብሮነት እጣ ፈንታችንን የተቃና ለማድረግ ከመጣር የተሻለ አማራጭ እንደማይኖረን ተራው አርሶ አደር ሳይቀር የሚገነዘበው ጉዳይ መስሎ ነው የሚሰማኝ።

ይሁን እንጂ ይህን ፈፅሞ ሊስተባበል የማይችል ነባራዊ እውነታ አምኖ መቀበል ውርደት የሚመስላቸው ፅንፈኛ ተቃዋሚ ፖለቲከኞች ብዝሃነትን በአግባቡ ስለማስተናገድ አስፈላጊነት የተናገረውን ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሁሉ፤ በአፍቃሪ ኢህአዴግነት እየፈረጁ ሊያሸማቅቁት ሲሞክሩ ማየት የተለመደ ጉዳይ ነው። እናም አንደኛ ዓመቱን በያዘው የሀገር አቀፍ ፓርቲዎች ፖለቲካዊ የድርድር መርሐ-ግብር ላይ የሚሳተፉ የተቃውሞው ጎራ ልሂቃን ከዚህ አኳያ የሚስተዋለውን የአመለካከት ዝንፈት በማቃናት ረገድ የማይናቅ ድርሻ ሊኖራቸው እንደሚችል ይታመናል። ስለዚህም ህብረተሰባችን መሰል የውይይትና የድርድር መድረኮች ለሀገራዊ ፖለቲካችን ችግሮች መቃለል ስለሚኖራቸው ፈርጀ ብዙ ፋይዳ ተገንዝቦ ማበረታታት

ይጠበቅብናል የሚል እምነት አለኝ። በተረፈ ግን የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ክራሞት፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ የጀመረቺው የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ሂደት ተጠናክሮ የሚቀጥል እንጂ የሚቀለበስ እንዳልሆነ የሚያረጋግጥ ተደርጎ ሊወሰድ እንደሚገባውም ነው ለኔ የሚሰማኝ። አበቃሁ !